የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፰
አዲስ አበባ የካቲት ፲፪ ቀን ፲፱፻፺፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

13th Year No. 18
ADDIS ABABA 19th Febuary, 2007

ማ ው ጫ

አዋጅ ቁጥር ፭፻፲፰/፲፱፻፺፱ ዓ.ም

ከፊንላንድ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጋር ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት የተደረገውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ…. ገጽ ፫ሺ፭፻፸፱

CONTENTS

**Proclamation No. 518/2007**

The Republic of Finland Agreement on the Promotion and Protection of Investment Ratification Proclamation …. Page 3579

### አዋጅ ቁጥር ፭፻፲፰/፲፱፻፺፱

### ከፊንላንድ ሪፐብሊክ መንግሥት ጋር ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት የተደረገውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በፊንላንድ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት እና ዋስትና ለመስጠት የካቲት ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም ስምምነት በአዲስ አበባ የተፈረመ ስለሆነ፤

ስምምነቱ ሥራ ላይ የሚውለው በተዋዋዮቹ ሀገሮች ህጎች መሠረት መጽደቁን የሚያረጋግጡ ሰነዶች በዲፕሎማቲክ አካላት አማካኝነት ልውውጥ ከተደረገ በኋላ እንደሆነ በስምምነቱ ስለተገለጸ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥር ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እና /፲፪/ መሠረት ከዚህ እንደሚከተለው ታውጇል።

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ “ከፊንላንድ ሪፐብሊክ ጋር ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት የተደረገውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፭፻፲፰/፲፱፻፺፱” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### PROCLAMATION NO. 518/2007.

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT ON THE PROMOTION AND PROTECTION OF INVESTMENT WITH THE GOVERNMENT OF REPUBLIC OF FINLAND

**WHEREAS,** the Agreement on the Promotion and Protection of Investment between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Republic of Finland is signed in Addis Ababa February 23, 2006;

**WHEREAS,** it is stipulated in the Agreement that it shall enter into force on the date of exchange of instruments of ratification through diplomatic channel;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 6th day of February, 2007;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as "The Republic of Finland Agreement on the Promotion and Protection of Investment Ratification Proclamation No.518/2007."

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፪. ስምምነቱ ስለመጽደቁ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በፊንላንድ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል ኢንቨስ ትመንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት በአዲስ አበባ ከተማ፣ የካቲት፲፮ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም ላይ የተፈረመው ስምምነት ፀድቋል።

## ፫. የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ ኃላፊነት

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ የካቲት ፲፪ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 2. Ratification of the Agreement

The Investment Promotion and Protection Agreement signed in Addis Ababa on February 23, 2006 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Republic of Finland is ratified.

## 3. Power of the Ethiopian Investment Agency

The Ethiopian Investment Agency is hereby empowered to implement this Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall come into force up on Publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 19th day of February, 2007**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**